# አናጺው ዘለቀ

## (አጭር ልቦለድ)

ከኤፍሬም በቀለ

የሐምሌ ሥላሴዎች ዕለት!

ገበያ የለም! ደጁ ደግሞ ክረምት በክረምት፣ ዝናብ! ድጥ - ድጥ ዝናብ «ቅው! ቅው! ቅው! ቋ! ቋቋቋ!» ያደርገዋል - አናጺው ዘለቀ የሚሰማሩን አናት:: በጥቁር እጁ የተያዘው ፋስ መዶሻ እድልዎ አያውቅም:: ሁሉንም አመዳም ከንፈሩን ነክሶ፣ ጉልበቱን ሁሉ ለቀኝ እጁ አበድሮ አናት አናቱን ይጠቀጥቀዋል::

ፋቅ! ፋቅ! ፋቅ! ፋቅ! ያደርገዋል የየእንጨቱን ገላ፣ በግራ እጁ መሪነት፣ በቀኝ እጁ ጉልበት ፊትና ኋላ በሚያመላልሰው መላጊያ:: ለሚፍቀው የእንጨት ዓይነት አድልዎ አያደርግም:: ቀረሮው፣ ዝግባው፣ ጥዱ፣ ጥቁር እንጨቱም ሆነ ብሳናው፣ እንጨት እንጨት ነው፤ ጣውላውም ጣውላ:: ብቻ የጉብጠው እስኪታና፣ ሻካራው እስኪለሰልስ ይላጋል፣ ይጠረባል::

በዚህ መሐል ከእለታት አንድ ቀን አሮጌ ከተማ ካለው የገበያ ሱቅ ተንጠልጥላ ሳለ የነበራትን ነጭ ቀለም ካጣች ሁለት ሶሥት ዓመት ያለፉት የዘለቀ ሸሚዝ በላብ ርሳ ትጨቀያለች:: ጠርብ የሚያህል ሰውነቱ ካጐነበሰበት ድንገት ቀና ቢል፣ ጥልፍልፍ የጉማ ጫማ የተጫሙት እግሮቹ ከተቸከሉበት ለእፍታ ያህል ቢነቀሉ ምናልባት ዘለቀ ያላበሰውን እጁን ለማድረቅ መዶሻውን አስቀምጦ የቤቱን ፍርግርግ ግድግዳ ተደግፎ ወደ ቀመው ኩንታል ሙሉ ሠጋቱራ ሲያመራ ብቻ ነው:: መዶሻ መላጊያ ... ጣውላ ... እንጨት፣ ከንጋት እስከጀምበር ግባት ህይወቱ ያለው ህይወቱ ነው::

ከአናጺ ቤቱ ውጪ ላለው ዓለም ጀርባውን ሰጥቶ ፊቱን ወደግዳግዳው አዙሮ ለሙጣጭ ከቀረው የእንጨት ዘር ጋር ሲታገል የሰው ጥላ ይከብደዋል:: ትከሻውንና አንገቱን ወደበሩ አዙሮ ይመለከታል:: ነጭ ኩታቸውን አጣፍተው ለብሰው የባት ተሁለት ሱሪያቸውን ሁለት ግርጌዎች በአዲስ ዳርማር ጫማ ያስጌጡ ጠና ያሉ አዛውንት ይመለከታል::

«እኚህስ የዋዛ ሰው አይደሉም» ይላል ዘለቀ በልቡ፤ ወደ አናጺው ቤት ሲገቡ ቡሽ ባርኔጣቸውን እንኳ ለአመል ያህል ከፍ አለማድረጋቸውን በመመልከት:: ቱጃር ናቸው፤ ድሮም ገንዘብ በትዕቢት የማይደፍነው ልብ እንደ ሌለ በጨረፍታ ያሰላስላል::

አዛውንቱ የያዙትን ወፍራም የሽመል ከዘራ ቀስረው፣ «ይኼ ስንት ነው?» ይሉታል:: አጥሮ ከገዘፈው ሰውነታቸው ጋር ሲስተያይ የድምጻቸው ስላላነት ሳቅ ያጭራል::

ዘለቀ እጁን በሰጋቱራ አሽቶ ካደራረቀ በኋላ በግንባሩ የሚወርደውን ላብ አንዴ ሞዥለጥ አድርጐ ያብስና የአዛውንቱን ከዘራ ባለ ነሐስ ጆንፎ በአይኖቹ ይከተላል:: ከበሩ በስተግራ በኩል ግማሽ አካሉን ለወጪና ወራጁ አጋልጦ ያስቀመጠውን ባለ አራት እግር ጠረጴዛ ማለታቸው እንደሆነ ይገነዘባል:: ሰማይና ምድር ከተላቀቁ ያላላቀቃቸውን ወፍራም አመዳም ከንፎሮቹን አላቅቆ በምላሱ ያረጥብና ከነጋ ያልተነጋገረበትንና ከምራቁ በስተቀር ያልዋጠበትን ጉሮሮውን «እህህም» በማለት ለንግግር ካመቻቸ በኋላ፣ «ዋጋው አርባ ሽልንግ ነው» ይላቸዋል::

«ይህንን እኮ ነው የምልህ» በማለት አዛውንቱ ሁለቴ ከተራመዱ በኋላ በከዘራቸው ጠረጴዛውን ጉንተል ጉንተል ያደርጉታል::

ምን አይነቱን ልበ ድፍን በገድ ጣለበት? ደግሞ ንቀታቸውን መደበቅ አይችሉም መሰል አይኖቻቸውንም ፊታቸውንም ያስፀይፉታል::

«እኔም እሱን ነው ያልኩት:: እንዲያውም የዛሬ ሶሥት ሣምንት የሱን ወንድም አርባ ሰባት ሽልንግ ነው የሸጥኩት»

«ካያ ሶስት ብር ካምሳ?!» በማለት አዛውንቱ ከንፈሮቻቸውን ሽርመም ያደርጉታል:: «ይህን የሳሙና ሰንዱቅ ካያ ሶሥት ብር ካምሳ?! ሰውም ገንዘቡም አብዷል አትለኝም?!»

ከዝግባ እንጨት ያነጠው ጠረጴዛ ተዋርዶ የሳሙና ሰንዱቅ መባሉ ቢከነክነውም ንዴቱን መዋጥ ግድ ሆነበት:: መቼም ገበያ የማያመጣው ጉድ የለም:: የዛሬው ገበያ ደግሞ ነገረኛ፣ ሙጢ አፍ ከሆነ ሰው ጋር ነው ያጋፈጠው:: ነገረኛ ለመሆናቸው ጥርጥር የለውም:: ከንፈሮቻቸው ስስ ናቸው::

«ይበሉ ስንት ይወስዱታል?»

«ጠረጴዛህን ወድጄልህ እንዳይመስልህ!... ካልክስ የሚረባ አይደለም» አዛውንቱ ከዘራቸውን ከብብታቸው ሥር ሻጥ በማድረግ አጐንብሰው ጥንካሬውን ለመለካት ከጠረጴዛው ጋር ትግል ገጠሙ::

ምን አይነቱ የሰው ነገር የማይጥማቸው አንቋሻሽ ሰው ናቸው? ደግነቱ ጠረጴዛው ፍንክች አለማለቱ:: ዘለቀ የልብ ደስታ ተሰማው:: በጠረጴዛውና በአዛውንቱ መሐከል የተደረገውን ትግል በራሱና በአዛውንቱ መሐል የተደረገ የጉልበት ፍተሻ ውድድር አድርጐ ቆጠረው::

«ብቻ ምንም አይል፣ ለኩሽና አያንስም:: ለሴቶቹ ዕቃ ማስቀመጫ ይሆናቸዋል» አዛውንቱ በተጽናና ስሜት ወደ ዘለቀ ዞር አሉ::

«ግን ሃያ ብር ውድ ነው! ... የተቃጠለ ገበያ!» በግራጫ ረዥም ጺምና ሪዝ የተሸፈኑትን ስስ ከንፈሮቻቸውን አላቅቀው ፈልቀቅ ሲሉ ተመለከተ:: ሁለመናቸው ነጭ ነው ይበል? ኩታቸው፣ ጺማቸው፣ እጀጠባባቸው፣ ባተ ሁለት ሱሪአቸው፣ ሪዛቸው፣ ጥርሶቻቸው ሳይቀሩ ነጫጮች ናቸው::

«ከነጋ ገድ አላልኩም፣ የርስዎኑ ገድ ልሞክረው:: ሰላሳ ዘጠኝ ሽልንግ ይውሰዱት!»

አነጋገሩ «ሰሞኑን ከኪሴ ሰባራ ሣንቲም አልገባም» የሚል የመማጠን ድምጸት ነበረው::

«ሰውዬው ጤናም የለው? አያወጣም አልኩህ እኮ»

«አንድ ሽልንግ ወረድኩሎት እኮ ጌታው!»

«አሥር ትሸጠዋለህ ወይስ አትሸጠውም?»

ቃሉ ከአፋቸው ከመውጣቱ የዘለቀ ጥቁር ግንባር ቁጥር፣ ደፍጠጥ ያለው አፍንጫው ደግሞ ይበልጥ ዘርፈጥ አለ:: ምን አይነት ነትራካ፣ ነዝናዛ ሰው ናቸው በሉ? ይኼ አሁን የተጣላ ሰው ያስታርቃል? ... ሲገዛ ነው ዋጋ ሊሰብር የመጣው? ... የእንጨት ሸበት!

«አሥር ምን? ... አለ ዘለቀ በንዴት::

አሥር ብር! ... ሀያ ሽልንግ!» አዛውንቱ ለጠረጴዛው ግዢ የሰጡትን ብር ብዛት ለማመልከት የሁለቱን እጆቻቸውን መዳፎች ወደርሱ በመዘርጋት ጣቶቻቸውን አስቆጠሩት:: «አሥር ይሆናል ወይንስ አይሆንም?»

«አያዋጣኝም!» ዘለቀ አንገቱን በዝግታ ያወዛውዛል:: «የምገዛበትን የቁርጡን ልስጥህ!» በጉጉት ያፈጠጡት የዘለቀ ዓይኖች ዘር በማለት አዛውንቱ ጀርባቸውን ሰጡት:: ከነጭ ኩታቸው ሥር ወደሚገኘው እጀጠባባቸው የደረት ኪስ ቀኝ እጃቸውን በመስደድ የቆዳ ቦርሳቸውን በማውጣት ከውስጡ አንድ ቀይ የቀን መቁጠሪያ አዠንዳ ሳቡ:: አዠንዳው ተሸብልሎ የታሰረበትን ጥቁር ጥለት ከፈቱ በኋላ ጥቂት ብሮች መዘዙ::

ቀጥቃጣ ምን ያንቀጠቅጠዋል? ምን ገበያ ቢጠፋ ብር አይቶ የማያውቅ መሰለው?... ምነው በበጋው ጊዜ ቢሆን ኖሮ! ሰፍሳፋ ሽማግሌ! «እንካ ያዝ!»

አዛውንቱ ገንዘብ የያዙበትን እጃቸውን ሲዘረጉለት የብሩን ብዛት ተመለከተው:: ሁለት ባለ አምስትና ሁለት ባለ አንድ ብር ኖቶች ናቸው:: ሃያ አራት ሽልንግ ... ሰቀቀናም! ... በእንቢታ ገሸሽ አለ::

«ያዝ እንጅ፤ ቁጠረው!»

«አያዋጣኝም!»

«ቀድሞ ነገር መቼ ቆጠርከውና?!»

«በዚህ ዋጋ አልሸጠውም!»

«እሺ፤ ይሁን አሥራ ሶሥት!» ዘወር በማለት በግራ እጃቸው ከአጀንዳው አንድ ብር በማውጣት አከሉለት::

ሰፍሳፋ ሽማግሌ! አሁን በርሱ ቤት ገንዘብ ጨምሮ ሞቷል::

«ነግሬሀለሁ ኋላ እንዳይቆጭህ፤ ከዚህ ቤት ከወጣሁ ሁለተኛ አልመለስም!»

አዛውንቱ ወዲያውኑ ከግንባራቸውና ከጉንጮቻቸው የአጥንት ገደል ሥር የሚቁለጨለጩ ትንንሽ ዓይኖቻቸውን ያለ አድራሻ በቤቱ ውስጥ ሲያንቀዋልሏቸው ዘለቀ ተመለከተ:: ከአሥራ አምስት ቀን በፊት ሰርቶት ያልተሸጠለት አንድ የስኒ ረከቦት በስተቀር ሌላ የሚሸጥ እቃ እንደሌለው የዘነጋ ይመስል የአዛውንቱ አመለካከት ሌላ ዕቃ የመግዛት ፍላጐት መሆኑን በማወቁ ደስ ተሰኘ:: ግን ምን ዋጋ አለው? ሰቀቀናም ዋጋ ሰባሪ ሰው ናቸው:: ከፋው!

የአዛውንቱ ትኩረት እንደተመኘው ሁሉ በቅድሚያ ከስኒ ረከቦቱ ላይ አረፈ:: ግን አልቆየም:: ወዲያው በስተቀኝ፣ ከቤቱ ግድግዳ ጥግ ላይ ተነባብረው የተዘረጉትንና በላያቸው ላይ ድሪቶ አበሳ ያስቆጠረው አሮጌ ብርድ ልብስ የተቀመጠባቸውን ካርቶኖች ይመለከታሉ:: እነዚያን ስስ ከንፈሮቻቸውን ሸርመም ያደርጋሉ::

«ምነው ምነው፤ ድፍን አገር በተሞናሞነ የአጣና አልጋ ላይ የምታቀማጥል ሰው ከዚህ ትተኛ?... አሁን ማን ይሙት ለራስህ የሚሆን መኝታ የምትሰራበት እንጨት አጥተህ ነው?...

አይመልስላቸውም::

አዛውንቱ ለአይናቸው ማረፊያ የሚሆን ሌላ ነገር ያጣሉ:: ወንበር ይሰራል፤ ነገር ግን ከቤቱ ውስጥ አንዳችም መቀመጫ የለውም:: የየመንደሩ ጋለሞታ ተሰባስቦ ከአቦል እስከ በረካ ቡና ለሚቀዳበት ስኒ ረከቦት ያንፃል፤ ግን ጓዳ ከሌለው ቤቱ ስኒውም ጀበናውም የሉም:: የልብስ ሣጥንና የእቃ ቁምሣጥን ይገጥማል:: የለበሰውና ከመሬት ግድግዳው ላይ ከሰቀላት አንዲት ቅል ሌላ እቃ የለውም:: በቤቱ ውስጥ ያለው አንድ ጆንያ እንጨት ፍቅፋቂ ተሞልቶ ቆሟል:: ይህም የሌላ ሰው ምጣድ የሚያስማ የሌላ ምድጃ የሚያሞቅ ነው::

እራሱ ግን ምድጃውንም ምጣዱም የለውም:: ለአናጢው የተረፈው አመድ ነው:: ወለሉ አመድ... የእንጨት ፍቅፋቂ ብናኝ፣ ደጁ አመድ... የእንጨት አዋራ ... «ጠንቋይ ለራሱ አያውቅም» ይላሉ በመገረም::

ወድያው ቀና ይሉና ካዘመመው የቤቱ ጣሪያ ያፈጣሉ፤ የጥቀርሻ ቆርቆሮ የለበሰ ጣሪያ። ... መቼም ጥቀርሻውን ከኋላቸው እጆቹን አጣምሮ ከሚቅለሰለሰው አናጢ በፊት ቤቱን የተከራዩት ሰዎች የምድጃ ጪስ የፈጠረው መሆን አለበት። አናጢው እንደሆነ ለራሱ እሳት የሚባል አንድዶ አያውቅም። አዛውንቱ በአቦሰጡኝ እውቀታቸው ደስ በመሰኘት እዢያን ነጫጭ ጥርሶቻቸውን ይፈለቅቃሉ ደግሞ የሸረሪቱ ድር፤ አበስኩ ገበርኩ! ምናለ ቢጠርገው? ይገርማቸዋል።

«ምናለ ይህን የተወላገደ የቤትህን መስኮትና መዝጊያ ብትለውጠው?»

«ቤቱ የኔ አይደለም»

«ታዲያ የማነው?»

«የኪራይ»

«ቢሆንስ እስካለህበት የራስህ አይደል?» /...«ይሉና ፈገግ ይላሉ።

«እስካለህበት» እስከመቼ እንደሚኖርበት ከአንድዬ በስተቀር ዘለቀ አያውቀውም። ዕድሜው በአንድ ወር መጨመሩን እንኳን የሚያውቀው የቤቱ ጌታ ኮሳሳው ካቺሳ ዶጮ ሥላሴን ቆጥረው ደረታቸው ላይ ሲር... ሲርር ከሚለው አስም እየተናነቁ «ወር ከገባ ድፍን ሰባት...ኪራዩን አምጣ» ሲሉት ነው። አቶ ካቺሳ ብቅ ባሉ ቁጥር፤ በወር የሚከፍላቸውን ሃምሳ ሽልንግ ለመቀበል ሌላ ምክንያት የሚያሻቸው ይመስል «... ያቺ ክኒኔም አልታብኛለች» ማለታቸው ይገርመዋል።

አዛውንቱ ትከሻቸውን ከፍ ከፍ ያደርጉና ያንን ነጭ ኩታቸውን በማስተካከል «አልሸጥልህ አልከኝ አይደል?» ይሉታል።

«ሃያ ስድስት ሽልንግ አያዋጣኝም»

«እኮ አሥራ ሶሥት ብር ነው የማያዋጣህ? ክረምት መሆኑን ዘነጋኸው መሰል!»

በግራ እጃቸው የያዙትን ከዘራ ወደ ቀኛቸው ያዞሩና ፊትፊቱን ትክ አድርገው ይመለከቱታል። በልቶ የሚያድር አይመስልም። ጉንበስ ብለው ያደረጉትን ጫማ ያስተውላሉ። ከዚህ አናጺ ፊት ይልቅ ዳርማራቸው ዓይን ይስባል።

«አዎ! አያዋጣኝም፤ ቢያዋጣኝ ምንቸገረኝ?»

«በል ተወው አሥራ ሶሥት መስጠቴም የጠዋት ገበያ ነው ብዬ ነበር። ... ምናልት ከሄድኩ በኋላ መሸጥ ቢያስኝህ ቤት ድረስ አምጣልኝ። አቶ ወልደየስ ቦሩ ጠጅ ቤት ካልክ ትንሽ ትልቁ ያሳይሀል።» ደህና ዋል ሳይሉት የቤቱን ጉብን ሲራመዱ ከቆመበት ሆኖ በዝምታ ሸኛቸው።

ገበያ ከጠፋ ሰነበተ። ወደ እንጨት መላጊያው አግዳሚ ተሰፋ ባጣ አካሄድ እግሮቹን እየጎተተ ተራመደ። ወደ አናጺ ቤቱ የሚመጣው ሁሉ አውርቶ ተንተርኮ ሐጅ ነው። እህል ባፉ ባልዞረም። የአቶ ካቺሳ ዶጮም ሃምሳ ሽልንግ በእጁ አልገባም። ያለው እንጨትም የጀመራትን የእንጨት ሳጥን እንኳ አያስጨርሰውም።

ሜትሩን አንድ ቁራጭ ባውላ ሊለካ እንደዘረጋ ስሙ ሲጠራ ይሰማል። «!... ዘሉ!» ትለዋለች ከወደላይ መንደር ከምትገኘው ኩራዝ ቤት የመጣች ሴተኛ አዳሪ።

ጉብቷ ተፈጭቶ የተመረገበት እስኪመስል ድረስ ፊቷ በማድያት ጠቁሯል። ደግሞ ዘመዶቿን ውኃ ፈጅቶባታል መሰል፤ የተቀባችው ኮኮስ ቅባት ከጉያዎቿ ከሚወጣው ትንፋግ ጋር ተዋህዶ አፍንጫ ይሰነፍጣል። ሁለት የፊት ጥርሶቿ ወልቀዋል።

«ምን ፈለግሽ?» አላት ዘለቀ ደርሶ የምትፈልገውን የማያውቅ ይመስል።

ፈገግ አለች፤ ደግሞ መሳቂያ ጥርስ እንዳለው ሰው። አፍዋ ደግሞ ማድ ቤት ይመስል ጥቀርሻው!

«ዘሌ እቁቤ እኮ ዛሬ ነው»

የደላት! ደግሞ እቁብ ትላለች። ይኼን ጊዜ የሶሥት ሽልንግ እቁብ እየጠጣች ይሆናል። የሰው ችግር የማይገባት፤ ድሮም የዱቤ ነገር ይኼው ነው። ትንፋሽ እስኪያጥራት «እሰይ... ዘሌ! ... ዘልዬ!» ስትል እንዳላደረች ሁሉ አምስት ሽልንጉን ልትቀበል መጣች። ከትናንትና ቀን አንስቶ ከሁለት መለኪያ ካቲካላ በስተቀር እህል የሚባል ነገር ጉረሮው እንዳልዋጠ አይገባትም።

ደግሞ ሻሿ ተንጋድዷል። በጠዋቱ በዚያ ቋቋትያም የአጠና አልጋዋ ላይ ከአንዱ ጋር ተላፍታለች። ታዲያ ከርሱ የተቀበለችውን አትከፍልም? ወይስ በዱቤ ነው የጋለባት? መጋኛ ይጋልባትና።

« በል እንጂ፤ ምን ፀጥ ትላለህ?»

«ታቦቱ /ትንሽ ቆይተሽ ... ተመለሺ።»

«ምን ትፎግራለህ? እቁቡን የምጥለው በስንት ሰዓት ነው ብዬ ነግሬህ አልነበረም? አሁን ሰባት ሆኗል። ይቀጡኛል። በዚህ ላይ እጣዬም ይታጠፍብኛል።»

ዝም ብሎ ያያታል፡፡ ደህና አንበጣ ናት፡፡ የምትበላውን ሁሉ የት ነው የምታደርሰው? ወይስ እንደርሱው እህል ባፍዋ አልዞረም? አጥንቷን በአዲስ ሻማ ሸፍናዋለች፡፡ ሠናና?... በዱቤ ባይሆን ኖሮ አቅፈው የሚተኟት አይደለችም፡፡

«ዘሉ! በል እንጂ!»

«ኋላ ተመለሺ አልኩሽ እኮ!»

«አትገግም!»

«አሁን ስለሌለኝ እኮ ነው ታቦቴ!»

«ምን?! የለኝም? ... የአባትህ ማሳ አደረግከው እንዴ?»

ሸንጧን በሁለት እጆቿ ይዛ ትምነቀነቅ ጀመር፡፡ «በልመና እግሬን ብትልስ አዝኜ ባሳድርህ ጉድ ታደርገኛለህ?»

«ስለሌለኝ ነው፡፡ ከራስሽ ክፈይና በኋላ ብቅ በይ!»

«ከነጋ አልሸቀልኩም፤ ዱዲም የለኝም»

«ታዲያ ምን ይሻላል? ተበድረሽ ክፈያ!»

«ክረምት መሆኑን አጣኸውና ነው? ማን ያበድረኛል?»

በዓይኖቿ ቤቱን መበርበር ጀመረች፡፡

«ታቦቴ! ሰሞኑን በሙሉ ገበያ ጠፍቶ እኮ ነው!»

«ለምን አይጠረቀምም?! ታቦቴ ያባት እዳ የለባትም!»

ዓይኖቿ በሩ ጥግ ላይ ከተቀመጠው የሲኒ ረከቦት ላይ አረፉ፡፡

«እንጨት እንኳ መግገር አጥቼ ሥራ ማቆሜ ነው»

«ስትፎግረኝ ነው እንጂ እውነት ገንዘብ አጥተህ ነው?»

በወላቃዋ ፈገግ አለች፡፡ እንደምታስጠላ ማን በነገራት?

«ታቦቴ ሙች የለኝም፤ የጀመርኳትን ሣጥን እንኳ የምጨርስበት እንጨት መግገር አጣሁ እያልኩሽ?»

ወደ ዘለቀ ፈጠን ብላ ተራመደች፡፡

«ልፈትሽህ!»

በምንቸገረኝ ትከሻዎቹን ከፍ ዝቅ አድርጐ የተማረከ ወታደር ይመስል እጆቹን ወደላይ አነሳላት፡፡

በቀኝ ኪሱ ቀዳዳ የሾለከው እጇ ከሞቃት ጭኑ ጋር ተገናኘ፡፡

ቱ! ሙታንቲ እንኳ የለውም፡፡ ከዚህ ጋር ነው ያደረችው? ያውም በዱቤ! አፈር ያስበላው የአባቷ ውቃቤ...

ብብቶቹ ሳይቀሩ ፈተሸችው፡፡ ስንዱቅ መሰሏት ይሆን?

«ቀድሞውኑ ልፊ ሲልሽ ነው፤ እያለኝ የለኝም አልልሽ!»

በዝምታ የስኒ ረከቦቱ ላይ ስታፈጥ ትንሽ ቆየች፡፡

«አሁን የለኝም ማለትህ ነው፤ አይደል?»

«እያየሺው?»

ከመቅጽበት ተፈናጠረች፡፡ የስኒ ረከቦቱን ከተቀመጠበት አንስታ ተፈተለከች፡፡ ተከተላት፡፡ አልደረሰባትም፡፡ እነዚያ ማማሰያ እግሮቿ ለሩጫ ነው የተፈጠሩት፡፡ ተስፋ ቆርጦ ቆሞ በአፉ ደረሰባት፡፡

«ታቦቴ! ነግሬሻለሁ! ብትመልሽ ይሻልሻል! አሥር ሺልንግ ነው ዋጋው!»

«ፋራህን ፈልግ! አራዳ ለአራዳ ምን ያጣላናል በሰው በረንዳ!...

ታቦቴም እንዳንተው ምላጭ ናት!» በአንድ እጇ የስኒውን ረከቦት አንጠልጥላ በሌላው ደግሞ ሸንጧን ይዛ በርቀት ቆማ ተወዘወዘችበት፡፡

«ኋላ እንዳንጣላ! አሥር ሽልንግ ነው ዋጋው!»

«ጤቦ ከፈለግክ ማታ መጥተህ መልሱን ታድርበታለህ»

ከልብ! ከላባ! ... ጅኒ! ሰይጣናም መለኮን! ለሷ የሚሆን ሌላ ቅጣት ምን አስፈለገው? ይምሽ ብቻ! ሞትኩ እስክትል ያሻታል፡፡

ወደ ቤቱ ተመልሶ ገባ፡፡ አዛውንቱ ያራከሱበት ጠረጴዛ ብቻ ነው የቀረው፡፡ ቢያጣ ቢያጣ ሰላሣ ሽልንግ ያወጣል፡፡ ሆዱ ደግሞ እረ የእህል ያለህ ይላል፡፡ የደላው፤ የባለቤቱ ችግር የማይገባው፡፡ ሆዳም፡፡ በአንድ መለኪያ ግምቢቹ አረቂ ማቃጠል ነበር፡፡

ወደ አናጢ ጠረጴዛው አመራ፡፡ ለአዋይ የቀረችውን እንጨት መትሮ መመገዝ ቀጠለ፡፡ ከሁለት ቀን በፊት የመጽሐፍት መደርደሪያ ሠርቶ እንዲያመጣለት ያዘዘው አስተማሪ ትዝ አለው፡፡ ምን ዋጋ አለው? እንጨት የለም፡፡ እነዚህ አስተማሪ የሚባሉ ጉዶች ደግሞ ያለመጽሐፍ መደርደሪያ በቀር የሚያሰኛቸው ሌላ እቃ የለም፡፡

ዘወር ብሎ ጠረጴዛውን ተመለከታት፡፡ ሰላሳ ሽልንግ ቢሸጣት እንኳ... በሁለት ሽልንግ አዲስ ከተማ ወጥቶ እራቱንም፣ ቁርሱንም፣ ምሣውንም አንድ ወፍራም ዶኬ ይልፍበታል፡፡ በአንድ ሽልንግ አሮጌ ከተማ ተመልሶ አራት ብርሌ የስኳር ጠጅ ይከልሰበታል፡፡ ከዚያ ደግሞ ማታ እዚያች ታቦቴ የሚሏት ወላቃ መለኮን ዘንድ ይሄዳል፡፡

በመጋዙ ተቆርጦ የወደቀውን ጉማጅ ተመለከተ፡፡ የመጨረሻው እንጨት ነው፡፡ ለሣጥኑም ማጠፊያ አልተገዛለትም፡፡ አንድ አሥራ አምስት ሽልንግ ያስፈልገዋል፡፡ ጠረጴዛውን ከሚሸጥበት ሰላሣ ሽልንግ ውስጥ የማጠፊያውን፣ የዶኬውን የጠጁን ሂሣብ አነሳለት፡፡ አሥራ ሁለት ሽልንግ ይተርፈዋል፡፡ ...

ስሙ ሲጠራ አዳመጠ፡፡ ክው ብሎ ደነገጠ፡፡ ለካስ ስላሴዎች ኖረዋል፡፡ የምን ዶኬ?... የምን ጠጅ?... የምን ጣውላ? ... የምን ማጠፊያ? የአቶ ካቺሣ ዶጮ ባለቤት እትዬ ሰርካለም በራፉ ላይ ተከምረዋል፡፡ ወደል ናቸው፤ ኮሳሳው ካቺሣ መጥኔውን ይስጣቸው፤ ፊታቸው ብቻ እንሥራ ያህላል፡፡ ደግሞ ብርድ እንዳይገባቸው ነው መሰል ወፍራም ጋቢ ለብሰዋል፡፡ ብርድ በምናቸው እንዳይገባ ይሆን? ቆዳቸውን ቢዘልቀው ስባቸው አያሳልፈው፡፡ ጉማሬ!

«ደህና ዋልክ ልጅ ዘለቀ?»

ድምፃቸው ደግሞ መሽከሩ! መላጊያ ያስፈልገዋል፡፡ አሁን እንዴት እንደዋለ መጠየቁ ምን ይረባል? የመጡበትን ሀምሣ ሽልንግ አምጣ ማለቱ አይሻልም፡፡? አሣማ! ወይስ ባዶ ሆዱን አድሮ መዋሉን እንዲነግራቸው ይፈልጋሉ?

«ደህና ዋሉ እትዬ ሰርካለም?» ፀጉሩን በጣቱ ይቆፍራል፡፡

«መቼም ወድጄ አይደለም!...» እህእ! ወድደው አይደለም፡፡ በግድ ተይዘው ነዋ ኪራይ ለመጠየቅ የመጡት፡፡ አቤት! አቤት! አዛኝ ቅቤ አንጓች፣ ደግሞ ወድጄ አይደለም!... ይልቅ የመጡበትን ተናግረው ቢለይላቸው አይሻልም? ምን ዙሪያ ጥምዝ ያስጋልባቸዋል? የለኝም ነው የሚላቸው፤ ቤቱን ልቀቅ ነው የሚሉት!

«ምን ትንሽ ቢሆን፣ እዳ እዳ አይደል?»

ሆሆይ/ ትንሽ? ... ሀምሣ ሽልንግ ነው ትንሹ? የደላት! ጠረጴዛው ሰላሳ ሽልንግ ቢያወጣለት እንኳን ሌላ ሃያ ሽልንግ ያስፈልገዋል፡፡

እትዬ ሰርካለም የለበሱትን ጋቢ ገልጠው አገር ከሚያካክሉ ጡቶቻቸው ስር ከረጢት ያወጣሉ፡፡ ሴትየዋ ምን ነካት? አበደች? ገና መክፈል አለመክፈሉን ሳታጣራ የፍርድ ቤት መጥሪያዋን በከረጢቷ ቋጥራ መጣች?

«ልጅ ዘለቀ! አትቆጣ! ቢቸግረኝ ነው!»

«እትዬ ሰርካለም! መቼም ክረምቱን ያውቁታል፡፡ ገበያም ገንዘብም ተያይዘው ጠፉ!»

የከረጢቱን ሽምቀቅ የሚፈታውን የእትዬ ሰርካለምን ወፍራም እጅ በአይኖቹ ይከተላል፡፡

«እኮ ይህንኑ አውቄ አይደል አትቆጣ ያልኩት? ... የክረምት ገንዘብ ትንሽ የለውም»

ወድያውኑ ከከረጢቱ ውስጥ ሁለት ሽልንጎች ያወጣሉ፡፡ የዘለቀ ዓይኖች በአድናቆት ያፈጣሉ፡፡

«ባለፈው ወር ማርያምን ስደግሥ የወሰድኩት የሁለት ኩንታል ስጋቱራ እዳ ነው!»

ሊጮህ ምንም አልቀረው፡፡ ሥላሴዎች በነፍስ ደርሰውለታል፡፡ ሁለመናው በደስታ ተፍለቀለቀ፡፡

«እግዚአብሔር ይስጥልኝ እትዬ ሰርካለም!»

«ላንተው ይስጥህ ወንድሜ! እኔ ምን አደረግኩልህ?»

ከስንት ድንጋጤ እንደገላገሉት አላወቁም፡፡ አቶ ካቺሣ እስኪመጡ ድረስ ስላሴዎች በዕለተ ቀናቸው አንድ ነገር ይጥሉለት ይሆናል፡፡

«ቢሆንም የክረምት ገንዘብ አይደል?» ይሉትና ድምፃቸውን ያለሰልሱበታል፡፡ «ልጅ ዘለቀ እንዳሁኑ አላቆይብህም፡፡»

ዓይናቸው ወደ ሠጋቱራው ኩንታል ሲወረወር ይመለከታል፡፡ «ከሶሥት ቀን አሳሳልፍብህም፡፡ ምጣድ ልጥድ ተነስቼ ሠጋቱራውን ባይ ባዶ ሆነብኝ»

«ግድ የለም /ይውሰዱ/» በጥፍሩ አናቱን ያርሰዋል፡፡

አንድ ሽልንግ ለመበደር ሁለት ሽልንግ ይዘው በመምጣታቸው እየተደነቀ ሠጋቱራውን ወደ ደጅ በማውጣት ያግዛቸዋል::

ወደ ቤት ተመልሶ ቆርጦ ያስቀመጣትን የመጨረሻ ጣውላ ከሣጥኑ ላይ ገጠማት::

ቀጥ አለ:: እንጨት የለም፣ ማጠፊያ የለም፣ ሥራ የለም፣ ገበያ የለም፣ ... ያለ ነገር የለም::

ዕለቱ ሥላሴዎች:: በኪሱ ሁለት ሽልንግ አለ:: ... ሆዱ አለ፣ ጉረሮው አለ፣ አቶ ካቺሣ ዶጮ አሉ፣ ... የሌለ ነገር የለም::

አቶ ካቺሣ ዶጮ በኃሳቡ ይደቀኑበታል:: የአስም ክኒናቸው ማለቁን ነግረውት የቤቱን ኪራይ እንዲሰጣቸው ይጠይቁታል:: እንደሌለው ይነግራቸዋል፣ እንዲታገሱት ይለምናቸዋል:: ኮሳሳው ካቺሳ እንደሆኑ በገንዘብ የመጣባቸው ሰው ደመኛ ጠላታቸው ነው ::የአናጺ እቃውን ቀምተው ከቤታቸው ያባርሩታል:: መጠጊያ ያጣል :: እንደኩሊዎቹ በረንዳ ይወድቃል:: ... ስብሃት ለአብ!

በፍርሃት ካሽማቀቀው የኃሣብ ህልሙ ሲነቃ የፈረደባትን ጠረጴዛ ያፈጥባታል:: ገደቢስ ናት ከተሰራች አሥራ አምስት ቀኗ አለፈ:: አልተሸጠችም:: ብትሸጥ እንኳ ኖሮ ግማሽ እዳውን ከፍሎ የካቺሳ ዶጮን ትዕግስት መለማመጥ ይችል ነበር::

ባለመጽሐፍ መደርደሪያው አስተማሪ ትዝ ይለዋል:: እንዴት ያማረ መደርደሪያ እንደሚሰራ ይነድፋል:: ምን ዋጋ አለው? እንጨትም መደርደሪያም የሉም::

አመለኛ ሆዱ ይሞረሙረዋል:: የሰው ችግር የማይገባው ደደብ! ጠረጴዛይቱ ላይ ያፈጣል:: የጠዋቱ አዛውንት፣ አቶ ወልደየስ ቦሩ ታወሱት:: ሣያ ስድስት ሽልንግ አያዋጣም:: ቢሆንም ምን ይደረግ፣ ሰው ወድዶ ይከስራል?... ማደሪያ ከማጣት፣ በረንዳ ላይ ከዱርዬዎች ጋር ከመጋፋት ይበልጣል?

አራት እግሯን ይዞ ብድግ አደረጋት:: ትከሻው ላይ ሲያደርጋት አልከበደችውም:: እንደተሸከማት በሩን ዘግቶ ከመንገድ ገባ::

አቶ ወልደየስ ቦሩ ቢኮሩበት፣ ቢዘባነኑበት እውነት አላቸው:: ግቢያቸው የታጠረበት ቆርቆሮ፣ ከንችና ማገር ብቻውን አምስት ዛኒጋባ ቤት ያስቀልሣል:: በስተግራ በኩል ካለው የጠጅ አዳራሽ ውስጥ የሚሰማው የጠጪዎች ሁካታ የአዲስ ከተማውን ገበያ ምሥጋና ያሳጣዋል:: ሴትና ወንድ አዝማሪዎች እየተቀባበሉ ሲንጉሩ ይሰማል:: ከጠጁ አዳራሽ በስተቀኝ ፈንጠር ብሎ ደግሞ ጉድ የሚያስኝ ግንብ ቤት ጉብ ብሏል:: ሁለመናው እንደባለቤቱ ነጭ ነው:: አጀብ ነው:: ታዲያ አቶ ወልደየስ ያልተንቀባረሩ ማን ይንቀባረርበት:: አፋቸውን አውጥተው ሲለምኑት አልሸጥም ያላቸውን ጠረጴዛ እንኳ ተሸክሞ አመጣላቸው አይደል?

ከአጥር ግቢው መግቢያ ላይ ደግሞ አቤት! ... የጣውላ ክምር! ሰማይ ሊነካ ምንም አልቀረው:: የዘለቀ አይኖች በአድናቆት ተበለጠጡ ... ምራቁን ዋጠ:: አንዱን ጣውላ እንኳ ቢሰጡት አስተማሪው ሥራልኝ ያለውን ጥሩ የመጽሐፍ መደርደሪያ ሰርቶ በጥሩ ዋጋ ይሸጠዋል:: እጅህ ከምን? የሚሉትን አቶ ካቺሳን፣ ከሃምሣ ሽልንግ ይላቸዋል::

የመኖሪያ ቤቱን በራፍ ሲያንኳኳ የከፈተችለት ልጅ ክንፍ ቀራት እንጂ መልአክ ትመስላለች:: ፊቷ እንደማሽ ያበራል:: ዳሩ፣ ብርንዶ እየበላች ጠጅ እንደ ውኃ እየጠጣች አድጋ ለምን አያበራ?... ንፍጥ የለ፣ ለሃጭ የለ!

«አቶ ወልደየስ ቤት አሉ?»

«ማ! ... አባይዬ?»

ደግሞ አነጋገሯ መጣፈጡ ... ዳሩ፣ በማር በወተት አድጋ ለምን አይጣፍጥ?

«አዎ! ጠርተውኝ ነበር!»

«ለምን፣ ቅድም ነው የወጣው!»

«እሜቴስ?»

«ማ እማይዬ?»

አይኖቿ ደግሞ ሲቁለጨለጩ ሲያምሩ

«አዎ እማዬሽን»

«ማነው እሱ የሚነታረከው?... የሉም፣ ጠበል ሄደዋል!» ከወደውስጥ የሰማው ድምጽ መረን ያደገ አዋቂ አነጋገር መሆኑ ያስታውቃል:: አንዲት ጠብደል ወጣ ብላ የልጅቱን ትከሻ በእጇ ገፋ አድርጋ አስገባቻት::

ለንቦጫም ነች:: ከርሳም መሆኗ ያስታውቃል:: በእጇ የገደል ስባሪ የሚያክል ዳቦ ይዛለች:: ጉንጮቿ ተወጥረዋል:: አበላሏን እንኳ ብታሳምረው ምን ነበረበት? ጥርሶቿ ዳቦውን ሲከረትፉት የመንደር ውሻ የምትጠራ ያስመስላታል:: ሰላቢ! የረሳውን ሆዱን አስታወሰችው::

«ምን ፈለግክ?»

የሰው ቂጣ ልቧን በጥጋብ ደፍኖታል፡፡ መልኳም፣ አነጋገሯም አስቀያሚ ነው፡፡ ስትኮሳተር ያን ጨለማ ፊቷን ይበልጥ ታጨልመዋለች፡፡ ደንደሳም!

«አቶ ወልደየስ ይህን ጠረጴዛ እንዳመጣላቸው አዘውኝ ነበር!»

«ታዲያ ማድ ቤት አስገባዋ»

ስድ! ስድ አደግ ነች! እንዴት እንዴት ያደርጋታል? ደግሞ በነዚያ ጫንቡስ ዐይኖቿ ጠረጴዛውን እንዴት ገላመጠችው? ... ትዕቢተኛ ወደል

«ገንዘቡን ...»

«ምዎ! ሰው የለም ተባልክ እኮ!»

«ቶሎ ይመለሱ ይሆን?»

«ጠብቃቸዋ!»

ተከትሏት በጓሮ በመዞር ጠረጴዛውን ማድ ቤት አስቀምጦ ወጣ፡፡ ከዋናው ቤት የጓሮ መግቢያ ደረጃ ላይ እህል ውሃ የማያሰኝ ቆመጥ የያዙ ሽማግሌ ቆመዋል፡፡ አላዩትም፤ ሰላምታም አልሰጣቸውም፡፡

አቶ ወልደየስ መጥተው ገንዘቡን ሳይቀበል መግቢያ አይኖረውም፡፡ ኪሱ ውስጥ ሁለት ሽልንግ ይቅጨለጨላል፡፡ ውጪ ቆሞ ከሚጠብቃቸው ወደ አዳራሹ ጉራ ብሎ ጠጁን ፉት እያለ መጠበቅ ይችላል፡፡ ብታንስም ትበቃለች፡፡ ገንዘብ ያለው መግቢያ አያጣም፡፡

ወደ ጠጅ ቤቱ ከመታጠፉ በፊት ያንን ክምር ጣውላ ተመለከተ፡፡ አቤት አቤት፤ ከየት አመጡት? አናጺው ዘለቀ ቤት የጠፋ እንጨት የነጋዴውን፣ የወልደየስ ቦሩን ግቢ አስጨንቆታል፡፡

ጠጪ ከሌለበት በረንዳ ላይ ተቀመጠ፡፡ አሳላፊው ገበያ በዝቶበታል፡፡ አናጺው ሱቅ የጠፋ ገበያ እዚህ ይዋከባል፡፡ ተዋክቦ ያዋክባል፡፡ እጆቹን ለጥሪ አጨበጨበ፡፡

አሳላፊው ብቅ አለ፡፡ ሰማያዊ ካፖርት ለብሷል፡፡ በአንድ እጁ ነጭ ማንቆርቆሪያውን በአንዱ እጁ ጣቶች ደግሞ አምስት ብርሌዎች ይዟል፡፡ ፊቱና ማጅራቱ ሳይቀሩ እንደቦረና በግ ሰብተዋል፡፡

ገና እንደተቀዳለት አንዷን ብርሌ በጉሮሮው ላይ አሳቃት፡፡ እንዴት ተጠምቷል? አሳላፊው ሳይመለስበት ደገመ፡፡

የአጥሩን መግቢያ ይመለከታል፡፡ አቶ ወልደየስ ብሩ ብቅ አላሉም፡፡ ደግሞ ያ ጣውላ እንደተከመረ ነው፡፡ ጠጁን ጨልጦ በባዶው ብርሌ መጠጫውን አግዳሚ ደበደበ፡፡ ስለስ፡፡

አራተኛውን እንዳስቀዳ፣ ከምመላለስ ብሎ ነው መሰል፣ አሳላፊው በሌላ ሁለት ብርሌዎች ቀድቶለት ተመለሰ፡፡ ወይ ጥጋብ! ዳሩ ለምን አይጠግብ? የአዳሜን ስሙኒ ሲለቅም ይውላል፡፡ ከየሰው የተራረፈውን ጭላጭ አንቡላ አጠራቅሞ ይሸጣል፡፡ በዚህ ላይ የአቶ ወልደየስ ቦሩን ትርፍራፊ ይጉስጉሳል፡፡ ልክስክስ!

ቀኑ ጨለመ፡፡ በአጥሩ በር ላይ ቢያፈጥጥም አቶ ወልደየስን የበላ ጅብ አልጮኸም፡፡ አቶ ካቺሳ ዶጮ ይታዩታል፡፡ ሥላሴዎች በዕለተ ቀናቸው ሊያዋርዱት ነው፡፡ ሁለት ሽልንጎቹን ለአሳላፊው ይከፍለዋል፡፡ አሳላፊው መልስም ሳይሰጠው ሽልንጎቹን ተቀብሎ ፊቱን ያዞራል፡፡ ሞሽላቃ! ይህቺም ገንዘብ ሆኖ ሊሰርቀው ነው?

«ኤ! ስማ! መልስ የለኝም እንዴ?»

«ስድስት እኮ ነው የጠጣኸው!»

«እኮ! ስሙኒ የለኝም?»

«የብር ስድስት ነው ጌታው!»

«ወደል! ሥላሴዎች ያፈንዱት!

ጠጂቱ እግሩን ያዝ አድርጋዋለች፡፡ በሁለት ሽልንግ ስድስት ብትሸጥም አትከፋም፣ ወስፋት ከተት ታደርጋለች፡፡ ገድገድ እያለ ከበረንዳው ይወርዳል፡፡ የአጥር ግቢው በር ክፍት ነው፡፡ ወደዚያው ያመራል፡፡

በጣውላው ክምር ላይ ያፈጣል፡፡ አንዱ ጣውላ ብቻውን አንድ የመጽሐፍ መደርደሪያና አንድ ሳጥን ይወጣዋል፡፡ ዞር በማለት የአቶ ወልደየስን ግቢ ተመለከተ፡፡ ጭር ብሏል፡፡ ጉንበስ ብሎ የእንጨቱን ዝርያ መመርመር ጀመረ፡፡ ጨለማው እንደልብ አያሳይም፡፡ አንዱን ጣውላ ከክምሩ ስቦ በማውጣት ብርሃን ወደአለበት ወስዶ መመልከት ቀጠለ፡፡ የዋንዛ ጣውላ ነው፡፡ አቤት ጥንካሬው! ከዚህ የታነጸ ጠረጴዛ ከገደል ላይ ቢወረውሩት ፍንክች አይልም፡፡ ዋጋውስ ቢሆን? የትና የት ነው!

«በህግ አምላክ! በህግ! .... ሌባ! ሌባ!»

ጣውላውን በእጁ እንደያዘ ደርቆ ቀረ፡፡ ከአቶ ወልደየስ መኖሪያ ቤት የጓሮ በረንዳ ላይ ቆመው የተመለከታቸው ሽማግሌ እብድ የሚያክል ቆመጥ ይዘው ወደርሱ ይሮጣሉ፡፡

«ሌባ! ሌባ! ሌባ!

የዋናው መኖሪያ በር ተከፍቶ ያቺ ደንደሳም ወደርሱ ትከንፋለች። በእጇ የብረት ዘነዘና ይዛለች።

«ኡኡ! ኡ! ኡ! ሌባ! ሌባ!»

ከጠጁ አዳራሽ ጠጪው ይግተለተላል፤ ወደርሱው። ባለቆመጡ ሽማግሌ አጠገቡ እንደደረሱ የበሉ የጠጡትን ያህል ያሳርፉበታል። እግንባሩ ላይ... እንደተሸነቆረ በርሜል ደሙ ይንፎለፎላል። ምድር ሰማዩ ይዞርበታል።

«አይናውጣ ሌባ! ገና ሳይመሽ?»

«ፖሊስ! ፖሊስ ይጠራ!»

ሰውነቱ ከድቶት ቀስ በቀስ ሽብረክ እያለ ከመሬት ላይ ይነጠፋል። ፖሊስ ጣቢያ አድርሰውት ከአንድ የሚቀረና ክፍል ይወረውሩታል።

አቶ ካቺሳ! ... አቶ ወልደየስ! ... ባለመደርደሪያው አስተማሪ! ... ያቺ ወላቃ መለኮን! ... ያቺ ደንደሳም ገረድ ... ያቺ መልአክ የመሰለች ልጅ ... ለዱቤ የተቀማው የስኒ ረከቦት! ... በጅምር የቀረው ሳጥን! በነፃ የሄደው ጠረጴዛ ... የአዲስ ከተማው ዶዬ! ... የአቶ ወልደየስ ጠጅ! ሁሉም በዐይኖቹ ላይ ይንከራተታሉ።